# ፓርኮቻችን የእድገት መሰላሎች

ታከለ አለሙ

በሀገር ደረጃ የጀመርነው የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርኮች ስራ ለሀገራችን ታላቅ ለውጥና እደገት ያስገኛሉ ተብለው ተስፋ የተጣለበት ነው፡፡ ግብርናችን ባሕላዊና ኋላቀር በመሆኑ የዝናብ ጠባቂነትን መንፈስ በሕዝባችን ውስጥ በማሳደሩ የተለዩ አማራጮችን መከተል ተስኖን ለድርቅና ለተመጽዋችነት ተጋልጠን ኖረናል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያን የመሰለ በተፈጥሮ የተለያየ የአየር ንብረት የታደለ ሀገር የለም፡፡

የብዙ ታላላቅ ወንዞችና ሀይቆች ባለቤት ሁነንም ከድርቅ ከረሀብ ሳንወጣ ረዥም ዘመናት አልፈዋል፡፡ በአጭሩ ለድህነታችን ለረሀብና ለድርቁ ዋናው መንስኤ ማንንም ሳንወነጅል እኛው ሁነን ኖረናል፡፡ እንደ አሁኑ ዘመን እንዴት ከኃላቀር ግብርና እንውጣ? እንዴትስ ወንዞቻችንን እንጠቀምባቸው? እንዴትስ ሌሎች ሀገሮች በረሀ የሆነ የአየር ንብረት ይዘው መልማት ቻሉ? ሕዝባቸውንስ ለመመገብ ለማኖር በቁ ብሎ ጠይቆ መፍትሄ ማበጀት ትልቅ ሀገራዊ እድገት ያስገኛል፡፡

እልም ባለው ንዳድ በረሀ አንዲት ጠብታ ውሀ በማትገኝበት ሰው ሰራሽ የምድር ለምድር ጥልቅ የውሀ ጉድጓድ ቆፍረው ሀገሩን ውሀ በውሀ ያደረጉት ሊቆች ጥምን ማሸነፍ የቻሉትስ እንዴት ነው፤ይሄን ማድረግስ የተቻላቸው ምስጢሩ ምንድነው ብሎ የሚጠይቅ ሀገሩን ለማልማት የሚተጋ ትውልድ ሳንፈጥር ብዙ ሺህ ዘመናትን አንቀላፍተን ኖረናል፡፡

የእኛ ምሁሮች ነፍስና ስጋ ያለው ሀገርና ሕዝብ እንዴት ከድህነት ይውጣ ? እንዴት ሀገራችንን በተደጋጋሚ የሚያጠቃትን ድርቅና ረሀብ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ እናስወግደው ወይም ሲከሰት ሕዝባችን እንዳይጎዳ እናድርግ የሚለው አይደለም የሚያስጨንቃቸው፡፡ የእነሱ ነፍስና ስጋ ከፖለቲካና ከተቃውሞ ጋር ብቻ አብሮ የተሰፋና የተጣበቀ ነው፡፡ፖለቲካ ብቻውን ሀገር አያለማም፡፡ከድህነት አያወጣም፡፡ ለሕዝቡ ዳቦና እንጀራ ቤትና መጠለያ አይሆንም፡፡

የተለያዩ ሀገራት ከድህነት ወደስልጣኔ ምኩራብ የተሸጋገሩት በምሁራን ልጆቻቸው አዳዲስ ሀሳብ አፍላቂነት ነው፡፡ለተከሰተው ችግር የሚመጥን መፍትሄ ማምጣት በቻሉና በሚችሉ ልጆቻቸው ነው፡፡ለድርቁም ለረሀቡም ለኃላቀርነቱም ወዘተ፡፡ለችግሮች ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ መፍትሄ ፈውስ መድሀኒት ማግኘት መቻል፡፡ይሄ ነው ለእኛም የሚበጀን፡፡

እንግዲያውማ ኢትዮጵያ በድህነት አቅምዋ ስንት ስንት ልጆችዋን አስተምራ ሊቀ ሊቃውንት ደረጃ አድርሳ ስታበቃ ሰበብ አስባብ እየፈለጉ ለሀገሬ ልስራ የቤተሰቤንና የሕዝቤን ውለታ ልመልስ እውቀቴን ሀገሬ ላይ ላውለው ሳይሉ በታላላቅ ሀገራት በብዙ ውድ የሙያ መስኮች በግብርናው በቴክኒዮሎጂው በምርምሩ መስክ ተቀጥረው ለሰው ሀገር የሚሰሩ ሳይንቲስቶች ኢትዮጵያውያን ሞልተው ተርፈዋል፡፡

ለሀገር ለሕዝብ መስራት ከድህነት ማላቀቅ የአደገች ሀገር እንድትሆን እውቀትን በስራ ማዋል የሚጠበቀው ከልጆችዋ ነበር፡፡ይሁን አሁንም ሀገራችን በመልካም ሁኔታ እየተራመደች ነው ያለችው፡፡የግብርናውን ዘርፍ አዲስ በተጀመረው የግብርና ፓርክ አሰራር እንዲሰራ ማድረጉ ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋግረናል፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ 17 የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርክ የሚገነባባቸው አካባቢዎች ተለይተዋል፡፡በሙከራ ደረጃ በአማራ፣ኦሮሚያ፣ ደቡብና ትግራይ ክልሎች አራት ፓርኮችን ለመገንባት ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ከተማ ለሚገነባው የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርክ በቅርቡ የመሰረት ድንጋይ ማስቀመጣቸውም ይታወሳል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በወቅቱ እንደገለጹት ፓርኩ ለዘመናት ከኋላ ቀር አሰራር ያልወጣውን የግብርና ዘርፍ ወደ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋግራል፡፡የቡሬ ግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርክ አንድ ሺ ሄክታር መሬት ስፋት ያለው ሲሆን በቅድሚያ በ260 ሄክታር መሬት ላይ እንደሚገነባ ተገልጿል።

ፓርኩ ሲጠናቀቅ የአካባቢው አርሶአደሮች በሰፊው ከሚያመርቱት ማሽላ፣ ስንዴ፣ ሰሊጥ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ማር፣ የእንስሳት ተዋፅኦዎችና መሰል የግብርና ምርቶች በግብዓትነት በመጠቀም እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያዎች የሚያቀርብ ሲሆን ለፓርኩ ግንባታ የሚያስፈልገውን 184 ሚሊዮን ዶላር የፌዴራልና አማራ ክልል መንግስታት በመደቡትና ከሌሎች አለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች በሚገኝ ድጋፍና ብድር እንደሚሸፈን ታውቆአል፡፡

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት፣ ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬትና በሌሎች የግብርና ሀብቶች ከአለምና ከአህጉሪቷ ቀዳሚ ከሚባሉ አገሮች ተርታ ብትሆንም ለኢንዱስትሪዎች ግብአት የሚውል ምርት በሚፈለገው ልክ እያመረትን አለመሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል፡፡ በምክንያትነት የተጠቀሰው አርሶና አርብቶ አደሮች በሳይንሳዊ መንገድ ያለማምረታቸው፤ ለተመረቱ ምርቶች የግብይት ሰንሰለቱ ዝቅተኛነት፣በሚመረቱ ምርቶች ላይ እሴት እየጨመሩ ወደ አለም ገበያ ያለመላክ ችግሮች ናቸው።

የአርሶና አርብቶ አደሮችን ምርታማነትን ከሚያሳድጉ ተግባራት ጎን ለጎን ምርቶችን በግብአትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ማስፋፋት አስፈላጊ ሲሆን ይህም በገጠር ሃብት ለመፍጠርና ኢኮኖሚው እንዳይናወጥ ለማድረግ እንደሚያስችል ጠ/ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ፓርኩ የአካባቢው አርሶ አደሮች ተጨማሪ የግብርና ምርቶችን እንዲያመርቱ ማስተማመኛ ከመስጠቱም በላይ በአካባቢው የምርት ዋጋ መቀዛቀዝን ያስቀራል፤ከአንድ ዓመት በኋላ ግንባታው የሚጠናቀቀው የቡሬ ግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርክ እስከ 100 ኪሎ ሜትር ዙሪያ ያሉ አርሶ አደሮችን ምርት በግብአትነት ይጠቀማል፤በቀጣይም መራዊ፣ እንጅባራ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ቻግኒ፣ ዳንግላ፣ በአማኑኤልና ሞጣ የገጠር የግብርና ምርቶች ማዕከል የሚቋቋሙ ሲሆን የሞጣ ማዕከል ግንባታ መጀመሩን ገልጸዋል፡፡

ፓርኩ የሚገኝበት ምዕራብ ጎጃም ዞን በእንስሳትና ሰብል ምርቶች ከፍተኛ አቅም ካላቸው አካባቢዎች የመጀመሪያው ነው፡፡በዓመት ከ32 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሰብል ምርት የማምረት አቅም አለው፡፡ከስድስት ሚሊዮን በላይ የእንስሳት ሀብት ባለቤት መሆኑን ከዞኑ የተገኘ መረጃ ይገልጻል፡፡

ርእሰ መስተዳድሩ ፓርኩ በተያዘለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማቅረብ በአካባቢው ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች፣የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛና መሰል ተቋማት ከወዲሁ ዝግጅት እንዲጀምሩ ጠይቀዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዴኤታው ዶክተር መብራቱ መለስ በበኩላቸው መሰል ፓርኮች የገጠር ትራንስፎርሜሽን ስራችንን በፍጥነት ለማሳካትና በክልሎች ፍትሀዊ እድገት እንዲኖር አጋዥ ነው ብለዋል፡፡

የቡሬ ግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርክ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ ለ619 ሺ ሰራተኞች የስራ እድል ይፈጥራል፡፡በፓርኩ ተቀነባብሮ ወደ ዓለም ገበያ ከሚላከው ምርት በዓመት 14 ቢሊዮን ብር ገቢ እንደሚገኝ ይገመታል፡፡

በብሔራዊ ደረጃ ለሙከራ የሚገነቡ ሌሎች ሶስት የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርኮች ዘንድሮ ወደ ግንባታ ይገባሉ፡፡በምዕራባዊ ትግራይ፣በኦሮሚያ ክልል ቡልቡላ፤ደቡብ ክልል ይርጋለም ተመሳሳይ ፓርኮች ለመስራት የግንባታ መሰረተ ድንጋይ የማኖር ስነስርአት እንደሚካሄድ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ትልቅና ግዙፍ ሀገራዊ የእድገት ስኬት መሰረት እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡

ማጠቃለያ

የዘመናዊ ግብርና ፓርኮች ግንባታ በሀገራችን ታሪክ አዲስ ነው፡፡በግብርናችን አሰራርና አመራረት ውጤት እጅግ ከፍተኛ ለውጥ በማምጣት የሀገሪቱን ግብርና ወደዘመናዊ ዘዴ እንደሚያሸጋግረው ይታመናል፡፡ወደ አለም አቀፉ ገበያ እንድንገባም ይረዳል፡፡ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ስራ ነው፡፡